# ኳስ ጨዋታና ፖለቲካ

## ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ

**ማስታወሻ ፤**

> ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የትግራይ ሕዝብ በወያኔ አገዛዝ አለመጠቀሙን ለማሳየት ኢትዮሜዲያ ላይ አንድ ጽሑፍ አውጥቶ ነበር ። ይህ የኔ ድርሰት የዚያ ተቃራኒው አስተያየት ስለሆነ መውጣት የሚገባው ፥ እዚያው ኢትዮሜዲያ ላይ ነበር ። ግን የኢትዮሜዲያ ባለቤት "በዚህ ድርሰትህ የትግራይን ሕዝብና ሕወሐት/ኢሕአዴግን አንድ አድርገሃቸዋል ("... TPLF a synonym with the Tigrai people.") ብሎ ሊያወጣው አልፈቀደም ። በእኔ አስተሳሰብ ይኸ ድርሰት ወያኔንና የትግራይን ሕዝብ አንድ አያደርግም ።

ወደ ተነሣኡበት ልመለስና ፥ እግር ኳስ ጨዋታ አጥብቄ እወዳለሁ ። እንግሊዞች ፉትቦል ፥ አሜሪካኖች ሶከር የሚሉትን ጨዋታ ማለቴ ነው ። አሜሪካኖች ለምን ሶከር እንደሚሉት ምክንያቱን ለማወቅ አልሞከርኩም ፥ አላሰብኩበትምም ። በዚህ ጨዋታ ፍቅር የተነደፍኩት ፥ በልኩ እንዳደርገውም ብዙ የተቀጣሁበት ፥ ገና ፊደል ስቆጥር ነው ። ለብዙ ነገሮች ያለኝ ፍቅር እየቀዘቀዘ ፥ እየጠፉም ሲሄድ ለኳስ ጨዋታ ያለኝ ፍቅር ግን አሁንም ትኩስ ነው ። ዛሬ መጫወት ባልችልም ፥ ዋናዋናዎቹን የእንግሊዝና የእስፓንያ የጨዋታ ኅብረቶች (English Premier League and Liga BBVA) ጨዋታቸውን በቴሌቪዥን እከታተላለሁ ። እንግሊዞች በጦርነት ጊዜ ለኳስ ጨዋታ ያህል ጦርነት ያቆሙ ነበር የሚሉት ተረት እውነትነት ቢኖረው አይገርመኝም ። የወያኔ ባለጸጎችም የእንግሊዝ አገር የእሑድ ቅዳሜን ኳስ ጨዋታ ለማየት እንግሊዝ አገር ድረስ በረር ብለው የሚመጡትም የፍቅር ጉዳይ ሆኖባቸው ነው--እኛ በልጅነታችን አዲስ አበባ ካምፖሎጆ ("ካታንጋ" የሚባል ስም ከወጣለት ቦታ) ሄደን ተጋፍተን እንደምናየው ማለት ነው ።

የመግቢያ ዋጋ መክፈል ከቻልኩ ጀምሮ "ከካታንጋ" ጋር ተለያይተናል ። አሁን ከፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ፥ አንዳንዴም ከአቶ አርአያ አሰፋ ጋር ፥ የሳምንቱ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ስቴዲዩም አዘውታሪ ሆኜ ነበር ። እንዲያውም ለዚህ ጽሑፍ መንሥኤ የሆነኝ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም "የወያኔ ጥላቻ ፍሬ" በሚል ርእስ በቅርብ ጊዜ በኢትዮሜዲያ ያቀረበው አስተያየት ነው ። መስፍን ጽሑፉን ፥ "ወያኔ ለትግራይ ሕዝብ ሀብትንና ብልጽግናን አመጣ ብለው የሚያምኑ ሰዎች ብዙ ናቸው ፤ ወያኔ የሥልጣን ወንበሩ ላይ በመውጣቱ ትግሬዎች ሁሉ አልፎላቸዋል ተብሎ ይታመናል ፤ በተለይ በአውሮፓና በአሜሪካ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በዚህ ላይ የጠነከረ እምነት አላቸው ፤ . . . የትግራይ ሕዝብ መደህየቱ አልበቃ ብሎት ሲለምንም እየተሳቀቀ ነው" በማለት ይጀምራል ። ጥቂት እልፍ ብሎ ፥ " ትግሬነታቸው ብቻ እንዲህ የደላቸው በጣም ፣ በጣም ጥቂቶች ናቸው ፤ ስለዚህ በወያኔ አገዛዝ ትግሬ ሁሉ ተጠቅሞአል ማለት ከጉልህ እውነት ጋር የሚጋጭ ስሕተት ነው" ይላል ።

እንደ መስፍን "ንትርክ" ባልለውም እርግጥ በጉዳዩ ብዙ ቁም ነገር የሞላበት ፥ ማስረጃ የቀረበበት ውይይት አንብቤያለሁ ። ከሳሾቹ ብዙ ማስረጃ ስለሚደረድሩ ፥ "በወያኔ አገዛዝ የትግራይ ሕዝብ አልተጠቀመም" የሚሉ የወያኔ ደጋፊዎች ብቻ መስለውኝ አላመንኳቸውም ነበር ። የመስፍንን አቋም ስለማውቅ ፥ ጽሑፉን

ሳነበው ማሰብና “ተሳስቼ ይሆን እንዴ?” ማለት ጀመርኩ ። የትግራይ ሕዝብ ሳይጠቀም ተጠቅሟል ፥ እየተጠቀመ ሳለ አልተጠቀመም ማለት ከሁለቱ አንዱ ይቅርታ የሚያስጠይቅ ትልቅ ወንጀል ነው ።  በእኔ በኩል ፥ ወያኔዎች ብዙ ሰው ደሙን አፍሶ የታገለለትን ዲሞክራሲን በማፈን የኢትዮጵያን ሕዝብ ስላሳቀቁት ፥  በፍጹም ጥላቻ እጠላቸዋለሁ ። ሆኖም የመስፍንን ድርሰት ሳነብ ፥ ጥላቻዬ እውነቱን እንዳላይ ዓይኔን ጋርዶት  ይሆን ብዬ ፥ ቆም ብዬ መረጃዎቼንና አቋሜን መመርመር ጀመርኩ ።

የወያኔ ተቃዋሚዎች ያቀረቧቸው መረጃዎች ያሳደሩብኝን እምነት በጀመርኩት የኳስ ጨዋታ ምሳሌነት ልግለጽ ። ከፕሮፌሰር መስፍን ጋር ብዙ ጊዜ በሀገር ጉዳይ እንከራከር ነበር ። እንደማስታውሰው ፥ የተለያየ አስተያየት ይዘን ተነሥተን ውይይታችንን በተመሳሳይ አስተያየት ላይ እንጨርስ ነበር ። አሁንም እንደግመው ይሆናል ።

የክበብ ቡድኖች ኳስ ጨዋታ የወያኔን ፖለቲካ ለመረዳት አስተዋፅኦ አለው ። የአንድ ቡድን አባላት ፥ ሁሉም ከቡድኑ አባቶች ጀምሮ ፥ በከፍተኛ ደረጃ ይግባባሉ ። አይጥ (ጎል) የሚያገባው አንድ ተጫዋች ቢሆንም ፥ ውጤቱ የሁሉም ጥረትና ተራድኦ አለበት ። ጥቅሙም የሞላ ቡድኑ ስለሆነ ፥ ደስታውም ፤ ጭፈራውም ፥ ሽለላውም አብሮ ነው ። የቡድን አባቶችን የሚመርጡት አባላቱ ናቸው--በዘመድ ሳይሆን በችሎታው ። ማንም ተጫዋች የራሱን ቡድን የሚጎዳ ጨዋታ አይጫወትም ፤ ጥቅም ያስቀራል ፥ መልቲነት ያለበት ተጫዋች ቢኖርባቸው ሥራው በግላጭ በአደባባይ ስለሚታይበት ወዲያው ይባረራል ።

በግላጭ የሚያዩ የቡድኖች ደጋፊዎች ሁሉ ናቸው ።  እነሱም ጥቅመኞች ናቸው ። በቡድኑ ጨዋታ የሚደሰቱት ወይም የሚያዝኑትና የሚቆጡት ስለዚህ ነው ። መቸም ጥቅም በወርቅ ብቻ አይገመትም ። እንዲያውም እኮ ወርቅ ለጥቅም መግዢያ እንጂ ራሱ ብቻውን ከጌጥነት ያለፈ ፥ ብዙ ጥቅም የለውም ።

የአንድ የኳስ ቡድን ጥቅመኞች ምን ያህል ብዙ እንደሆኑ እናስብ ። ለምሳሌ ፥ የእንግሊዝ ፕሬሚየር ሊግ አባል ቡድኖች ደጋፊዎቻቸው ፥ እንደ ወያኔ መኳንንት ኢንግላንግ ድረስ እየበረሩ ለማጨብጨብ የሚያስችል የተዘረፈ ወርቅ ባይኖራቸውም ፥ ብዛታቸው እስከ ዓለም ዳርቻ ይደርሳል ። እንግሊዝ አገር ለተደረገ ጨዋታ ዓለም ዳርቻ ያሉ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች እስከመፈናከት የሚደርሱበት አለ ። ቡድኑ ደጋፊዎቹን እንዳያስቀይም ብዙ ይጠነቀቃል ። ካስቀየመ ፥ ደጋፊ ያጣል ፤ ይወድቃልም ።

ጥቅመኞቹ የጥቅም ደረጃቸው የተለያየ ነው ። ለምሳሌ ፥ ቡድኑ የክበብ ቡድን ከሆነ ፥ የቡድኑ ባለቤት ገፈፉን ያነሣል ። ተጫዋቾቹ ጥቅማቸውን የሚረከቡት የተገዙ ዕለት ነው ። “የጨዋታ ቡድን ባለቤት አለው” ማለት ፥ ባለቤቱ ከፈለገ ፥ ምንጊዜም ይሸጠዋል ፥ ይለውጠዋል ማለት ነው ። ተጫዋቾቹም ከየቦታው ተገዝተው የተጠራቀሙ የመርሰነሪ (Mercenary)ብጤዎች ናቸው ። ጀሌው ሕዝብ ግን አንድ ቡድን የሚደግፈው ቡድኑ ብሔራዊ ወይም የሱ ስለሆነ ሳይሆን ፥ የሱ መሆኑን በጭፍን አምኖ ነው--በእምነት ብቻ ።  አለዚያማ ፥ አዲስ አበባ ላይ ሆኖ ለሊቨርፑል ማጨብጨብ ትርጉም አይኖረውም ።

እስቲ በዚህ አንጻር ወያኔዎችንና ደጋፊዎቻቸውን እንያቸው ፤ ወያኔ እንደ አንድ የኳስ ቡድን ነው ። እያንዳንዱ አባል የገንዘብ ጥቅመኛ ነው ፤ ማስረጃዎቹ እንደሚያመለክቱት ፥ ሁሉም አይበለጽጉ መበልጸግ

በልጽገዋል ። ራሱ ቡድኑም ቢሆን ለገንዘብ የተገዛ ነው ይባላል ። በየደረጃው የሚጠቀሙ ጥቅመኛ ደጋፊዎች አሉት ። "ገገርዎቹ የወንዛችን ሰዎች ናቸው" ማለቱ ብቻ የሚያረካቸው ሞኞችና አደገኛ ጥቅመኞች ጥቂት አይደሉም ፤ ይኸም ጥቅም ነው ማለት ነው ። ዋናው ጥቅም ግን የተመሠረተው በኢኮኖሚው ላይ ነው ። የውስጥና የውጪ ዐዋቂዎች እንደሚነግሩን ፥ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ በወያኔ ደጋፊዎች እጅ ተይዟል ። የመንግሥት ቁልፍ ሥራ የሚሰጠው ለትግራይ ተወላጆች ነው ። አንድ ሰው ሥራ ሲጠይቅ የሥራ ማመልከቻ ይሰጠዋል ። በማመልከቻው ላይ ችሎታውንና ዘር ማንዘሩን እንዲመዘግብ ይገደዳል ፤ ማንነቱን ይናዘዛል ። በዚህ ዘዴ ለአድልዎ ይጋለጣል ።

መለስ ዜናዊ ፥ "አይሁድ የአሜሪካን ኢኮኖሚ እንደያዙት የትግራይ ልጆችንም የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ አሲዛቸዋለሁ" ብሎ የፎከረው በፉከራ አልቀረም ። ኢኮኖሚውን በጠቅላላ የሚያንቀሳቅሱ የትግራይ ወጣቶች በጥድፊያ እየተዘጋጁ ነው ። በመንግሥት ሀብት ወደ አሜሪካና ወደ አውሮፓ ስሙ-ጥር ዩኒቨርሲቲዎች የሚላኩ ተማሪዎች የትግራይ ተወላጆች ናቸው ። እነሱ እስኪደርሱ ፥ አንዳንዱን ሥራ ሌሎች ይዘውት ብናይ ሌሎችም ተጠቅመዋል አንበል ። ቦታ ጠባቂዎች ናቸው ። የትግራይ መሬት ጠፍ ስለሆነ ፥ በሰቲት ሁመራ ፥ ወልቃይት ጸገዴ ትግራይ ሆነዋል ። ከዚያ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ያልሆኑ ገበሬዎች ተባርረው የርሻ መሬታቸውን የትግራይ ተወላጆች ወርሰውታል ። የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በመብራት እጥረት ምክንያት በጨለማ በዳበሳ ሲያመሹ ፥ ትግራይ ውስጥ እንዲህ ያለ ችግር ከተወገደ ፥ ዓመታት አልፈዋል ። **ይህ ሁሉ ሐሰት ከሆነ ፥ አቋሜን እለውጣለሁ ።**

እውነት ከሆነ ፥ ታዲያ እንዴት ነው ፥ በወያኔ አገዛዝ የትግራይ ሕዝብ አልተጠቀመም ለማለት የሚቻለው? ምናልባት የዚህ ሀገራዊ ወንጀል ዜናው ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚኖሩት ታፍኖ ፥ በውጪ አገር ለምንኖረው ብቻ ተከሥቶ ይሆን? ሁኔታው የጠበንጃ ጠባይ ተገላቢጦሽ ሆነብኝ ። ጠበንጃ ድምፁን ማሰማት የሚጀምረው ተኳሹ ከቆመበት ቦታ ሆኖ ፥ የሚመታው ርቆ ሄዶ ነው ። የወያኔ አድላዊነት አዲስ ነገር አይደለም ። ኢትዮጵያ ውስጥ አልታፈነም ። የወያኔ ጥረት ፥ "ትግራይ እስክትለማ ኢትዮጵያ ትድማ" መሆኑ ውጪ ሀገር ለምንኖረው የደረሰን ኢትዮጵያ ውስጥ በሰፊው ተነግሮ ነው ።

መቸም አንድን ሕዝብ በአንድ ትውልድ ከዳር እስከዳር ማበልጸግ አይቻልም ። መስፍን "ትግሬዎች ሁሉ" እያለ "ሁሉ"ን የሚደጋግማት ስለዚህ ከሆነ ፥ እንስማማለን ። እንዲያውም ፥ "ሁሉ" ከቁም ነገር አይቈጠርም ፤ ለመወያያ ርእስነት ብቃት የለውም ። ሁሉም ቀርቶ ፥ ዘጠና በመቶው የትግራይ ሕዝብ እስኪያልፍለት ድረስ እንኳን ገና ብዙ ጊዜ ይፈጃል ። ጅማሮው ግን ተጀምሮ እየገሠገሠ ነው ። ፍሬ ማፍራትም ጀምሯል ። እስከዚያ ብዙ ትግሬዎች እንደብዙ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ድኾች ሲለምኑ መታየታቸው አይቀርም ። እትግራይ ውስጥ ቀርቶ ፥ በብልጽግና በዓለም አንደኛውን ደረጃ በያዘችው አሜሪካን አገር እንኳን ለማኞች ሞልተዋል ። ተአምራዊ የኢኮኖሚ ሥርዓት ካልመጣ በያዝነው ሥርዓት ፥ እስከተጓዝን ድረስ ፥ ክርስቶስ ፥ "ድኾች ሁል ጊዜም ከማህላችሁ ይኖራሉ" ያለው ፥ የማይሻር ቃል ሆኖ ይኖራል ።

"በወያኔ አገዛዝ የትግራይ ሕዝብ አልተጠቀመም" የሚል እምነት ያለው ሰው ማስረጃው የትግራይ ለማኞች በመንገድ ላይ ማየት ከሆነ ፥ አንድ የትግሬ ለማኝ ከብዙ ኢትዮጵያውያን ለማኞች ማህል እስከተገኘ ድረስ ፥ በእምነቱ ሊጸናበት ይችላል ። ዋናው ቁም ነገር ግን እንዲህ ነው ፤ **የወያኔ አገዛዝ ለትግራይ ሕዝብ ያደላል ወይስ አያደላም** ። አያደላም ለማለት የዓይን ምስክሮችን መካድ ፥ መለስ ዜናዊንም ውሸታም ማድረግ ይሆናል ። "ለትግራይ ማዳላትስ አዳልተዋል ፤ ግን ሕዝቡ አልተጠቀመም" ማለትም ይቻል ይሆናል ። ግን እንዲህ ያለውን ተቃራኒ አስተሳሰብ ማስታረቅ ቀላል አይሆንም ። እያዳሉለት ባይጠቀም ፥ ወያኔዎችን ከማዳላት ወንጀል ነፃ አያወጣቸውም ። ማዳላት አንዱን ጠቅሞ ሌላውን ጥቅም መንሳት ነው ።

ማዳላት አደገኛ በሽታ ነው ። ፍሬው ጥላቻ ነው ። የተዳላበት ወገን ዳኛውንም የተዳላለትን ወገንንም አብሮ መጥላት ፥ ከዚያም አልፎ ማቄምና ክፉ ነገር ማሰብን ያስከትላል ። የትግራይ ሕዝብ አልተጠቀመም ማለት የትግራይን ሕዝብ አስጠልተውታል ማለት ከሆነ ፥ እኔም እስማማለሁ ። ጥያቄው ይኸ ከሆነ ፥ በእንደዚህ ያለ ጊዜ ፥ "ይህ ሁኔታ እኮ የወንድማማቾችን መተላለቅ ያስከትላል" ብሎ መሥጋትና በፍጥነት መፍትሔ መፈለግ የማንም ኢትዮጵያዊ ግዴታ መሆን አለበት ። ለጥፋቱ ተጠያቂው የትግራይ ሕዝብ አይደለም ። የትግራይ ሕዝብ ፥ "እኛ የምንፈልገው ዕድላችን እንደጥንቱ ከሌላው ሕዝብ ጋር እኩል እንዲሆን ነው" ቢል የመሪዎቹን አርጩሜ አይችለውም ። እስታሊን የሶቪየት ዩኒዮንን በቴክኖሎጂ ለማራመድ ያደረገውን እናውቃለን ። ራሳቸው ትግሬዎቹም ወደመጀመሪያው ላይ ቀምሰውታል ። ("ፋሺዝም በትግራይ" የሚለውን የጋዜጠኛ ሪፖርት እናስተውሳለን ።) ስለዚህ ትኵረቱ መሆን ያለበት በደላቸውን እንዲያቆሙ ምክር በሚገባቸው በወያኔዎቹ ላይ ነው ። ወያኔዎችና ደጋፊዎቻቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሰላም እንዲኖር ከፈለጉ (ለመፈለጋቸው ምንም ምልክት አያሳዩንም) ዕርቅ ለማምጣት ዕድሉ ገና አላመለጠም ። ብቻ የሚያሳዝነው ፥ ኋላ ቀር ፖሊቲከኞች የሚነቁት ዕድሉ ካመለጠ በኋላ ነው ። ቅዱስ ዳዊት ፥ "ስሕተትን (በጊዜው) ማን ልብ ይላታል" ሲል ደምድሞታል ።

ወደኳስ ጨዋታው ምሳሌ ልመለስና ፥ የወያኔ ቡድን አንዳንድ ጊዜ በራሱ ጎል ላይ አይጥ ያስቆጥራል ። ባለቤቱን (ኢትዮጵያን) ስለከዳ ፥ የባለቤቱን ጥቅም ያላንዳች ይሉኝታ ያዝረከርካል ። አገሪቱን ወደብ-አልባ ማድረግ ፥ መርከቦቿን መሸጨ ፥ ጎሳዎችን ማጋጨት ፥ አገር መከፋፈል ፥ በኢትዮጵያ ሀብት የሌላ ሀገር ባንክ ማበልጸግ ፥ ዓባይን ለመገደብ ካይሮ ድረስ ሄዶ ማመልከቻ ማቅረብ ሁሉ በራስ ጎል ላይ ኳስ ማስገባት (አይጥ-በላ መሆን) ፥ ነው ።